# የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር "የኮንስትራክሽን ሕግ/ውል ዋና ዋና ገፅታዎች" በሚል ርዕስ ያዘጋጀው ዓውደ ጥናት ቃለ-ጉባዔ

- **የስብሰባው ቦታ፡-** ሰሜን ሆቴል
- **የስብሰባው ቀን፡-** ታኅሳስ 1 ቀን 2009 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 እስከ ቀኑ 6፡30 ሠዓት
- **ጽሑፍ አቅራቢ፡-** አቶ ፋሲል ታደሠ /የሕግ አማካሪና ጠበቃ እንዲሁም በመስኩ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሌክቸረር/
- **አወያይ፡-** አቶ ዜና ደባሱ /የሕግ አማካሪና ጠበቃ እንዲሁም በመስኩ የረዥም ጊዜ ልምድ ያላቸው ባለሙያ/
- **በስብሰባው ላይ የተገኙ፡-** የማኅበሩ አባላት፣ የሕግ አማካሪዎች፣ ጠበቆች፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ ኮንስትራክሽን ማኅበራት፣ ሌሎችም

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ታምራት ኪዳነማርያም የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውን ካስተላለፉ በኋላ ማኅበሩ በዕለቱ ያሰናዳው ትምህርታዊ ውይይት "Peculiar Features of Construction Laws/Contract" ወይም በአማርኛው ‹‹**የኮንስትራክሽን ሕግ/ውል ዋና ዋና ገፅታዎች**››ን በሚመለከት ሲሆን ጥናታዊ ጽሑፉም የሕግ አማካሪና ጠበቃ እንዲሁም በመስኩ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሌክቸረር በሆኑት በአቶ ፋሲል ታደሠ እንደሚቀርብ፤ አወያዩምየሕግ አማካሪና ጠበቃእንዲሁም በመስኩ ሰፊ ልምድ ባላቸው በአቶ ዜና ደባሱ መሆናቸውን በመግለፅ ሁለቱም ባለሙያዎች ፈቃደኛ ሆነው በመምጣታቸው አመስግነዋቸዋል፡፡ ትምህርታዊ ውይይቱን ያዘጋጁት የማኅበሩ የኮንስትራክሽን ሕግ ኮሚቴ ከተከታታይ የሕግ ትምህርት ኮሚቴ ጋር በመተባበር መሆኑን የጠቀሱት የማኅበሩ ፕሬዝዳንት በተከታታይ የሕግ ትምህርት ኮሚቴ ውስጥ አቶ ኃይሉ ቡራዩ፣ አቶ ጌዴዎን ወ/ዮሐንስ እና አቶ ሚካዔል ተሾመ በደንብ እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ ብለዋል፡፡ ማኅበሩ ከዚህ በፊት በኮንስትራክሽን ሕግ ላይ ውይቶችን ሲያዘጋጅ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የኮንስትራክሽን ሕግ ኮሚቴ ተዋቅሮ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ አውስተዋል፡፡ የዛሬው ውይይት ላይ የምታደርጉት የነቃ ተሳትፎ ለጽሑፉ መጎልበት ወሳኝ ሚና የሚጫወት መሆኑን ያስታወሱት አቶ ታምራት መድረኩን እና አወያዩ ክፍት አድርገዋል፡፡

## አቶ ዜና ደባሱ - አወያይ (የሕግ አማካሪና ጠበቃ እንዲሁም በመስኩ የረዥም ጊዜ ልምድ ያላቸው ባለሙያ)

ይህ ትምህርታዊ ውይይት በመዘጋጀቱ አወያዩ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበርን ካመሰገኑ በኋላ የ1972 ዓ.ም. ምሩቅ መሆናቸውን፤ በተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶች በተለያየ ደረጃ የሰሩና

በአሁኑ ጊዜ በግል እየሰሩ መሆናቸው ገልፀው ከጽሑፍ አቅራቢው አቶ ፋሲል ጋር የረዥም ጊዜ ትውውቅ እንዳላቸውና አብረውም መስራታቸውን ጠቅሰዋል፡፡ የግንባታ ሕግ (Construction Law) ትምህርት በሕግ ትምህርት ቤት መሰጠት የተጀመረው ከ1980ዎቹ ወዲህ መሆኑን አወያዩ አስታውሰው አቅራቢው አቶ ፋሲል በዳኝነት፣ በኮንስትራክሽን ኩባንያዎች በአማካሪነት መስራታቸውን፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በዚሁ የሙያ መስክ course outline በማዘጋጀት፣ በኢትዮጵያ የሕግ መፅሔት በመሳተፍ እንዲሁም በከተሞች ፕላን ኢንስቲቲዩትም ሰርተዋል ብለዋል፡፡ አወያዩ ፅሁፍ አቅራቢው በመስኩ የዳበረ ልምድ እንዳላቸው ከገለጹ በኋላ ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ከሌሎች ሥራዎች በበለጠ ሰፋፊ ሲቪል የምህንድስና ሥራዎች በተለይም የሕንፃ፣ የመንገድ፣ የባቡር መስመር፣ የግድብና የድልድይ ግንባታ ላይ እየተሳተፈች የምትገኝ መሆኑን ካስታወሱ በኋላ በዘርፉም የተለያዩ አለመግባባቶች የሚስተዋሉ መሆኑን ፅሁፍ አቅራቢው በርዕሰ-ጉዳዩ ላይ ያዘጋጁትን ጽሑፍ እንዲያቀርቡ በመጋበዝ መድረኩን ለአቶ ፋሲል ታደሠ አስረክበዋል፡፡

## <u>አቶ ፋሲል ታደሠ - ጽሑፍ አቅራቢ /የሕግ አማካሪና ጠበቃ እንዲሁም በመስኩ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሌክቸረር/</u>

አቶ ፋሲልየኮንስትራክሽን ሕግ ወይም ውል ዋና ዋና ገፅታዎች ወይም ልዩ ባህሪያትበሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ ትምህርታዊ ገለፃ የሚቀርብ መሆኑን አስታውሰው ወደ ዋናው ገለጻ ከመግባታቸው በፊት እንደ መግቢያ የተጠቀሙት የዲያቆን ዳንኤል ክብረት ‹‹የሁለት ሐውልቶች ወግና ሌሎች››በሚል ርዕስ2003 ዓ.ም. ከተፃፈ 6ኛ እትም መጽሐፍ ውስጥ ካገኙት አንቀፅበመጥቀስየጀመሩ ሲሆን ይዘቱም አፄ ቴዎድሮስ ግዙፍ ሳይሆን እጅግ ውብ የሆነ ቤተክርስቲያን ማሰራት ፈልገው ሊቃውንቱን ሰብስበው ሲያማክሩ ከቆዩ በኋላ ቀልባቸው የሳበው ሃሳብ ግን ለቤተክርስቲያኑ ግንባታ የሚያስፈልገው 150 (አንድ መቶ ሃምሳ) ሰው ሆኖ 50ው (ሃምሳው) ሰሪ፣ 50ው (ሃምሳው) ደንጓሪ ቀሪው 50 (ሃምሳ) ደግሞ አነዋሪ ይሆናል የሚል ሲሆን ሰሪው ድንጋይ፣ ጭቃና የግንባታ ዕቃውን ሰርተው የሚያቀርቡ፣ ደንጓሪው የቀረበላቸውን የግንባታ ዕቃ በአግባበቡ በመሰደር ሕንጻውን የሚሰሩ፣ሲሆኑ አነዋሪው በበኩሉ ዳንጓሪው የሚሰራውን ውጭ ሆኖ በመመልከት የተዛነፈውን፣ የተጣመመውንና የተበላሸውን እንዲስተካከል አስተያየት ይሰጣሉ የሚል ነው ካሉ በኋላአሁን ያለውም የግንባታዎች ሥራ ከዚህ ብዙም የማይለይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 2 (3) ላይ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ለሚለው ትርጓሜ ከዚህ እንደሚከተለው ይነበባል፦

*«የግንባታ ዘርፍ ሥራ» ማለት ከሕንፃ፣ ከመንገድ ወይም ከመሠረተ-ልማት ሥራ ጋር በተያያዘ የሚከናወን አዲስ የግንባታ፣ የመልሶ ግንባታ፣ ደረጃ የማሳደግ፣ የማፍረስ፣ የጥገና፣ የማደስ ሥራ እንዲሁም ተጓዳኝ የሆነና ከዋናው ስራ ያልበለጠ ዋጋ ያለው አገልግሎት ሲሆን፣ የመገንባት፣ በባለቤትነት የመያዝ፣ ሥራውን የማንቀሳቀስ፣ የማስተላለፍ ወይም የመገንባት፣ የማንቀሳቀስ የማስተላለፍ ወይም የመገንባት፣ በባለቤትነት የመያዝ እና የማንቀሳቀስ ውሎችን ይጨምራል፡፡*

ኮንስትራክሽን የሰው ልጅ ከመፈጠሩ ጀምሮ ከነበረው ትንንሽ ግነባታዎች ውስብስብ እስከሆነው ዘመናዊ ኪነሕንፃ ድረስ ያለው ሲሆን የጥንት ግንባታዎች ከጥንታዊ የሜሶፖታሚያ እና ከጥንታዊ ግብፅ ሥልጣኔ የሚጀምር የሰው ልጆች የለት ተለት ሥራ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን አስረድተው በኢትዮጵያ እየተገነባ ያለው የህዳሴ ግድብ ወይም እንግሊዝ እና አውሮፓን የሚያገናኘው ታናል ካናል እጅግ ረቂቅና ውስብስብ ናቸውብለዋል፡፡ በዚህ ውይይት ላይ የኮንስትራክሽን ውልና ኮንስትራክሽን ሕግ የሚሉ ሐረጎች በተለዋዋጭነት የምንገለገልባቸው መሆኑን ያስታወሱትአቶ ፋሲል የዛሬው ውይይት በዋናነት የኮንስትራክሽን ውል ዋና ዋና ልዩ ባህሪያቱ ላይ የሚያተኩር መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ልዩ ባህሪያቱ እንደሚከተለው ተብራርተዋል፡፡

1. **እያንዳንዱ ኮንስትራክሽን ፕሪጀክት የራሱ ልዩ ባህርይ ያለው መሆኑ** (Prototypical Nature of the Works):-አንድ ግንባታ ከሌላ ግንባታ በንድፍ፣ በጥሬ ዕቃ ግብዓት፣ በባለሙያ አሠራር፣ በቆይታ፣ በቀለም፣ ወዘተ እጅጉን የሚለያይበት አግባብ አለ፡፡ ለምሳሌ የዛሬ አራት ዓመት አካባቢ በአዲስ አበባ ከተማ ን/ሥ/ለፍቶ ክ/ከተማ በተለምዶ ጀሞ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ከተሰሩት የጋራ መኖሪያ ቤት ሕንፃዎች መካከል አንደኛው የዘመመበት ሁኔታን ማስታወስየህንን አባባበል ለማሳየት በቂነው ብለዋል፡፡
2. **በሂደቱ የሚሳተፉ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ወገኖች መኖራቸው** (numerous participants):- በአንድ የግንባታ ውል ላይ ብዙ ሰዎች ይሳተፋሉ በዚህም ከሌሎች ውሎች ይለያል ብለዋልፅሁፍ አቅራቢው፡፡ የግንባታ ውል ሲባል አሰሪውና ተቋራጩ ውል ከመፈራረማቸው በፊት መሃንዲሶች እና ሌሎች ባለሙያዎች የሚሳተፉሲሆንየኢትዮጵያ የሕንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 243/2003 ግንባታ ለመገንባት የግንባታ ፈቃድ የሚያስፈልግ መሆኑን ይደነግጋሉ፡፡በደንቡ አንቀፅ 2 (8) መሠረት የግንባታ ፈቃድ ማለት፡-

*‹‹የግንባታ ፈቃድ›› ማለት አንድ የሕንፃ ግንባታ ለማካሄድ ለሚፈልግ አካል ሕንፃውን ለመገንባት የሚያስችሉት ዝርዝር መስፈርቶች እንደተሟሉ በከተማው ሹም ተረጋግጦ ግንባታ እንዲካሄድ ፈቃድ መስጠቱን የሚገልፅ ማስረጃ ነው፡፡*

ከግንባታ ፈቃድ በተጨማሪ የሕንፃ ፕላን ወይም ዲዛይን እንደ ቦታው ደረጃ ምድብ ይወሰናል፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 2 (15) ላይ እንደተረገነመው፡-

*‹‹ፕላን›› የአንድን ሕንፃ መጠን፣ ዓይነትና ስፋት እንዲሁም ሕንፃው የሚሰራበትን ቁሳቁስ ና የአገነባብ ዘዴን የሚያሳይ ንድፍ ወይም ሞዴል ሲሆን የአርኪቴክቸር፣ የስትራክቸር፣ የሳኒተሪ፣ የኤሌክትሪካል፣ የሜካኒካል፣ የእሳት መከላከልና የሌሎች ሥራዎችን ንድፍ ሊያካትት ይችላል፡፡*

እነዚህ *ሥራዎች* ከተሰሩ በኂላ የግንባታ ወጪ ይሰላል፡፡ አቅራቢው እንዳስቀመጡት ይሄ ሁሉ *ሥራ* የሚሠራው አካፋና ዶማ ከመምጣቱ በፊት ነው፡፡ የዲዛይን *ሥራ* የሚሰራ ሰው የመድን ዋስትና እንዲጠራ ይደረጋል በመሆኑም የመድህን ወይም የኢንሹራንስ ድርጅቶች ይገባሉ በማለት አቶ ፋሲል አብራርተዋል፡፡

በመቀጠልም አሰሪው (client) እና ተቋራጩ (contractor) ለ*ሥራ*ው ይፈራረማሉ፡፡ ከዚያም ‹አነዋሪ› መሃንዲስ ይገባል፡፡ ከዚያም *ሥራዎች*ን ይበልጥ የሚያቀላጥፉ ንዑስ *ሥራ* ተቋራጮች ይገባሉ ያሉት አቶ ፋሲልንዑስ የ*ሥራ* ተቋራጮች (sub-contractors) ወደ *ሥራ* የሚገቡበትና የሚመረጡበት አግባብ በ2 (ሁለት) ከፍሎ ማየት እንደሚቻል፤ እነዚህም፡-

ሀ/ ዋናው ተቋራጭ እራሱ አማካሪ መሃንዲሱን ወይም አሰሪውን አስፈቅዶ ንዑስ *ሥራዎች*ን ሊሰጥ ይችላል፡፡

ለ/ ሌላው ንዑስ *ሥራ* ተቋራጭ የሚመርጠው አሠሪው (client) እራሱ የሚሆንበት አግባብ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ይህ ዓይነት የንዑስ *ሥራ* አሰጣጥ የኤሌክትሮሜካኒካል *ሥራዎች* ለምሳሌ እንደአሳንሰር (lift or elevator) የመሳሰሉ *ሥራዎች* ላይ የሚስተዋል መሆኑን ፅሁፍ አቅራቢው አስረድተዋል፡፡

በኮንስትራክሽን *ሥራ* ከሚሳተፉ መሃንዲሶች ባሻገር ዕቃ አቅራቢዎችም (suppliers) ተሳታፊ መሆናቸውን፤ ከነዚህም ወገኖች በተጨማሪየፋይናንስ ተቋማት የጨረታ ዋስትና፣ የሶስተኛ ወገን መድህን፣ የግንባታ መድህን፣ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና፣ ወዘተ አስፈላጊ በመሆናቸው

የባንክና የኢንሹራንስ ተቋማት በዚህ የኮንስትራክሽን ሥራ ውስጥ ባለድርሻ እንደሚሆኑ ፅሁፍ አቅራቢው አቶ ፋሲል ታደሠ አስረድተዋል፡፡ የዲዛይን ስራ በቅጂና ተዛማጅ መብቶች አዋጅ መሠረት ጥበቃ የሚደረግለት መሆኑ ደግሞ ሌላተጨማሪ አካል እንዲኖርየሚያደርግ መሆኑን፤በአጠቃላይ የግንባታ ሥራ ውስጥ የሚሳተፉ ወገኖች ቁጥር ከሌሎች ውሎች አንፃር ሲታይ በእጅጉ የበዙ ሰዎች ተካፋይ የሚሆኑበት እንደሆነና፤ ከነዚህም መካከል ዋነኞቹ ግንባታው ባለቤት (owner)፣ ዲዛይነር፣ የዲዛይነር አማካሪ፣ ግንባታው ስራ አስኪያጅ፣ ተቋራጩ፣ ንዑስ ተቋራጭ፣ ዕቃ አቅራቢ (supplier)፣ የግንባታ ሰርቬየር (quantity surveyor)፣ ባንኮችና መድህን ተቋማት፣ ወዘተ ተጠቃሽ ናቸው ብለዋል- አቶ ፋሲል፡፡

3. **የሥራ መለዋወጥ የሚጠበቅና የማይቀር ስለመሆኑ** (variations to the works are almost inevitable):- የኮንስትራክሽን ሥራ ውስጥ የሥራ variations, alterations, additions, changes and omissions ሊቀሩ የማይችሉ እንደሆንያብራሩትአቶ ፋሲል፤ የአሠሪው የሃሳብ ለውጥ፣ የመንግስት ጣልቃ ገብነት እንዲሁም በሌሎች ምክንቶች ሥራው እንዲለወጥ እንደሚደረግ አብራርተዋል፡፡ በፍትኃብሔር ሕጉ የመለዋወጥ መብትን ለአሰሪው የሰጠ ይሁን እንጂ በcommon law ሀገራት ግን ይህን የመለዋወጥ መብት በውል መሠረት እንዲወስኑ ለተዋዋይ ወገኖች ነፃነትን ሰጥተዋል ያሉት አቶ ፋሲል አንድ ታዋቂ ፀሃፊን በመጥቀስ የሥራ መለዋወጥን (variation) ከጦርነት አውድማ ጋር ያመሳስለዋል ካሉ በኂላ ኃሳቡን ይበልጥ ግልጽለማደረግየፍ/ብሔር ሕግ አንቀጽ 3031ን ጠቅሰዋል፡፡

   *<u>አንቀፅ 3031፡- አሰሪው የሚጠይቃቸው የሥራ መለዋወጥ (1) የአሠሪው መብት</u>*
   *የተጠየቁት የሥራ መለዋወጥ በቴክኒክ ረገድ ሊፈፀሙ የሚችልና የሥራውንም ጥንካሬ የማይጎዱ ከሆኑ አሠሪው አስቀድሞ ከተስማማበት የሥራ ዕቅድ አንድ አንድ መለዋወጥ እንዲፈፀሙ ለመጠየቅ ይችላል፡፡*

   ጽሑፍ አቅራቢው በኮንስትራክሽን ውሎች ላይ ሥራን የመለዋወጥ ሁኔታ down-to-earth ይቀመጣል ብለዋል፡፡

4. **የግንባታ ውል አፈፃፀም ረዥም ጊዜ የሚወስድ እና በግንባታው ላይ ግድፈቶች ዘግይተው ሊታዩ መቻላቸው**:- የግንባታ ውል ከሌሎች ውሎች ልዩ የሚያደርገው ሌላው ባህርይ ውሉ የሚፈፀምበት ጊዜ የረዘመ መሆኑና የሥራ ግድፈቶችየሚታዩት ዘግይተው መሆኑን ጠቅሰው የግንባታ ሥራዎች አብዛኛውን ጊዜ በውሉ በተባለበት ጊዜ የማያልቁ ሲሆን አንድም ጊዜ ማራዘሚያ፤ አንድም የተጨማሪ ክፍያ ጥያቄ የሚቀርብበት ሁኔታ መኖሩን በዝርዝር አስረድተዋል፡፡ ከጊዜ ብዛት የጥሬ ዕቃ ዋጋ መጨመር እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ መናር

ሊከሰት የሚችል ሲሆን ይህን ወጪ ማን ይሸፍናል የሚለውን በውል በማስቀመጥ መዳኝት የሚቻል ሲሆን ብዙ ጊዜ በግንባታ ውሎች ላይ escalation and risk allocation clause እንደሚኖር አቶ ፋሲል አስረድተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሕግ የተቀመጠ መድህን የመሆን ኃላፊነት መኖሩን ጸሐፊው አብራርተው በዋቢነትም የፍትኃብሔር ሕጉን አንቀፅ 3039ን ጠቅሰዋል፡፡

*<u>አንቀፅ 3039፡ ሥራ ተቋራጩ የሚሰጠው መድን</u>*

*(1) ሥራ ተቋራጩ ሥራውን ካስረከበበት ቀን ጀምሮ ስለ መልካም አሠራሩና ስለ ሥራው ስለ ጠንካራነቱ ለዓሥር ዓመት ጊዜ መድን ነው፡፡*

*(2) በዚሁም ጊዜ ውስጥ በስራ ጉድለት ወይም በተሰራበት መሬት ዐይነት ምክንያት በተሠራው ስራ ላይ ለሚደርሰው መጥፋት ወይም መበላሸት አላፊ ይሆናል፡፡*

*(3) ማናቸውም ይህን ጊዜ የሚሳጥር ወይም መድንነቱን የሚሽር የውል ቃል ሁሉ አይጸናም፡፡*

5. **የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ከፍተኛ በሆኑ አደጋዎች** (risks) **እና ኃላፊነት** (liabilities) **የተሞላ መሆኑ፡-** የኮንስትራክሽን ሥራ አደጋዎች የሚበዙበት በመሆኑ እነዚህን አደጋዎች ለማስተዳደር የሚያመቹ አንቀፆች በኮንስትራክሽን ውሎች እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡
6. **በግንባታው የታየው ጉድለት ምክንያት ወይም ምንጭ የዲዛን ወይንስ የአገነባብ?** (the interaction between liability for defective workmanship and for faults in design):- ሕንፃ ተገንብቶ ካለቀ በኋላ ወይንም በሚገነባበት ወቅት የሚታዩ ችግሮች የሚፈጠሩ ሲሆን ለነዚህ ችግሮች መፈጠር ምክንያት ዲዛይኑን የሰሩት መሃንዲሶች ሕንፃውን በገነቡ ሰዎች የሚያላክኩ ሲሆን ገንቢዎቹ ደግሞ ጥፋቱ የዲዛይነሮች እንደሆነ የሚናገሩበት አጋጣሚ ሰፊ መሆኑን ፅሁፍ አቅራቢው አስቀምጠዋል፡፡
7. **እጅግ በርካታ የሆኑ ሰነዶችን የሚያካትት መሆኑ፡-** የኮንስትራክሽን ውሎች ከሌሎች የውል ዓይነቶች አንፃር ሲገመገም ብዙ ሰነዶችን በአባሪነት የሚይዝ በመሆኑ ልዩ የሚያደርገው መሆኑን የጠቆሙት ፅሁፍ አቅራቢው የግንባታ ሥራ ውል ከመፈረሙ በፊት፣ ውሉ ሲፈረምና ከተፈረመ በኋላ ያሉ ለውጦችና መፃፃፎች በሙሉ የውሉ አካል መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡
8. **የውል ጠቅላላ ሁኔታዎች - የውል ልዩ ሁኔታዎች** (General (standard) conditions of contract-special conditions of contract):- ምንም እንኳን እያንዳንዱ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ሥራዎች በባህርያቸው ልዩ ቢሆኑም የግንባታ ሂደቶቹ እና የአስተዳደር ሥራዎች ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑ በኢንደስትሪው ውስጥ ወጥ የሆነ ስታንዳርድ (General

Conditions of Contract (GCC)) እንዲኖር ምክንያት ይሆናል በማለት የውል ጠቅላላ ሁኔታዎች መኖራቸው ጠቃሚ መሆኑን አቶ ፋሲልገልፀዋል፡፡ አቶ ፋሲልበኢንጂነሪንግ እና ኮንስትራክሽን ኢንደስትሪው ወጥ የሆነ የሥራ ውል ሁኔታ ፎርሞች ወይም ስታንዳርድስ ማዘጋጀት በ19ኛው ክፍለ ዘመን የተጀመረ መሆኑን የታሪክ ድርሳናት የሚያስረዱ መሆኑን ጠቅሰው ጁሊያን ቤይሊ የተባለ ምሁር የተናገረውን ‹‹It is rare to find a standard form that is masterpiece of clarity and workmanship.›› ካስቀመጡ በኋላ የግንባታ ውል ፎረሞች በቁጥርና በዓይነት እየበዙና እየሰፉ መምጣታቸውን አውስተዋል፡፡ በዘርፉ የተሰማራ ሌላ የኮንስትራክሽን ሕግ ምሁር ‹‹…construction could not function efficiently without the use of standardized construction contracts›› በማለት ያስቀመጠ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ፋሲል በእኛ ሀገርም ውስን መ/ቤቶች GCC አውጥተው ጥቅም ላይ የሚያውሉበት አግባብ መኖሩን ተናግረዋል፡፡

አቶ ፋሲል የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር (MoWUD) እና የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር (PPA) ያወጡት ጠቅላላ የውል ሁኔታዎች መኖራቸውንአስታውሰውበዓለማቀፍ ደረጃ ያለው ጠቅላላ የውል ሁኔታዎች (General (standard) conditions of contract) የሚያስቀምጠው ***Fédération Internationale Des Ingénieurs-Conseils***(FIDIC) እንደሆነና ቃላቶቹ ፈረንሳይኛ ቢሆኑም ምንጮቹ ግን ከወደ ሀገረ እንግሊዝ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ እነዚህ ስታንዳርዶች የኢንደስትሪ አቢዮትን ተከትለውየመጡበመሆኑ የኮመን ሎው ተፅዕኖ አለባቸው ብለዋል፡፡ የኮመን ሎው ሀገራት የህግ ባለሙያዎች ዝርዝር የሥራ ጉዳይን በውል ውስጥ በማተት የሚያስቀምጡበት የሕግ አግባብ ያለ ሲሆን የኮንቲኔንታል ወይም የሲቪል ሎው ሀገራት የሕግ ሰዎች የኮመን ሎው ሀገራትን ውል ቢመለከቱ በእጅጉ ሊደነግጡ እንደሚችሉ በመግለፅ በሲቪል ሎው ሀገራት የውሉ ዝርዝር የሚዳኘው በተፃፈ ሕግ ነው ብለዋል፡፡ ሌላው ፅሁፍ አቅራቢው ያነሱት ነጥብ ጠቅላላ የውል ሁኔታዎች (GCC) ያላቸው ውጤት ወይም ሕጋዊ ደረጃ (legal status) ምን ያህል እንደሆነ በጥያቄ መልክ አንስተዋል፡፡ ጽሑፍ አቅራቢው ጄኔራል ኮንዲሽንስ በመ/ቤቱ እንደሚወጣ የፍ/ብሔር ሕጉ አንቀፅ 3135 የሚያስቀምጥ የጠቀሙ ሲሆን ድንጋጌውም እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

*<u>አንቀፅ 3135 -ለአስተዳደር መሥሪያ ቤት ውሎች ተፈፃሚ የሚሆኑ ጠቅላላ ሁኔታዎች (ግዴታዎች) (1) የውሎች አጻጻፍ</u>*

*ሥራዎች የሚፈጸሙባቸውን አኳኋን የሚያመለክቱ ለአይነት የሆኑ ደብተሮችን (ካዬደሻርዥተፓ) ጠቅላላ ውለታዎችንና ደንቦችን የሚመለክቱ ደብተሮችን አጠቃላይ የሆኑ ውሳኔዎች ያሉባቸውን ደብተሮች ሥራው የሆነው እያንዳንዱ የአስተዳደር*

*መሥሪያ ቤት ሊያዘጋጃቸውና በሚኒስቴሩ ትዕዛዝ ሥራዎቹ የሚፈጸሙት በነዚህ መሠረት ነው ተብሎ ሊወሰን ይችላል፡፡*

ስታንዳርዶቹ በግልፅ የውሉ አካል ናቸው ካልተባለ ተፈፃሚነት እንደማይኖራቸው በፍ/ብሔር ሕጉ አንቀፅ 3138 ጽሑፍ አቅራቢው የጠቀሙ ሲሆን ድንጋጌውም እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

*<u>አንቀፅ 3138፡፡ (2) በውሉ ውስጥ የሚገኘው ቃል፡፡</u>*

*(1) ሥራዎቹ የሚፈፀሙባቸውን አኳኋን የሚመለከተው ደብተር ወይም ጠቅላላ ውለታዎችና ደንቦች ያሉበት ደብተር አተቃላይ የሆኑት ውሳኔዎች ያሉበት ደብተር አንድ ውል ሲደረግ ወደ እነሱ የሚመራ በግልፅ የተፃፈ ቃል ከሌለበት በቀር ስለውሉ አተረጓጎም ወይም በውሉ ውስጥ ስላለው ቃልና ስለውሉ አፈጻፀም በነዚህ ደብተሮች ውስጥ ለው ደንብ ተፈፃሚአይሆንም፡፡*

*(2) ……*

*<u>አንቀፅ 1686፡፡ (5) ጠቅላላ የሆኑ የሥራ አፈጻጸም ሂኔታዎች</u>*

*ባለውል የፈፀማቸው ጠቅላላ የጉዳይ ሁኔታዎች ሌላውን ተዋዋይ ወገን ሊያስገድዱት የሚችሉት አንደኛው ወገን እነዚህን ጉዳዮች አስቀድሞ ዐውቋቸውና ወዶ ተቀብሏቸው የተገኘ እንደሆነ ወይም የሕዝብ ባለስልጣኖች የደነገጓቸው ወይም ያፀኗቸው ሲሆኑ ነው፡፡*

Adhesive contract ላይ በትርጉም ረገድ አከራካሪ ነገር የተፈጠረ እንደሆነ ባለእዳውን በሚጠቅም መልኩ መተርጎም እንዳለበት የፍ/ብሔር ሕጉ የሚያስቀምጥ መሆኑን ያብራሩት አቶ ፋሲል በዋቢነትም የፍ/ብሔር ሕግ አንቀፅ 1738ን ጠቅሰዋል፡፡

*<u>አንቀፅ 1738 - ለባለዕዳው ምቹ የሆነ ትርጉም፡፡</u>*

*(1) የውሉ አኳኋን የሚያጠራጥር ሲሆን የሚተረጎመው በውሉ አስገዳጅ የሆነው በሚጠቀምበት ሁኔታ ሳይሆን በውሉ ተገዳጅ ለሆነው ሰው ምቹ በሚሆንበት አኳኋን ነው፡፡*

*(2) ቢሆንም በጠቅላላው ስምምነት በውል ዓይነት ወይም ለውል ፎርም ተመልክተው የሚገኙት ውለታዎች በአንደኛው ወገን ተዋዋይ ብቻ የተሰሩ ሲሆኑ*

የሚተረጎሙት እንዲቀበልና እንዲፈቅድ ለተጠየቀው ለውል ተቀባዩ ጥቅም ምቹ በሚሆንበት አኳኋን ነው፡፡

ይሁን እንጂ አቶ ፋሲል የኮንስትራክሽን ውሎች የAdhesive contract ባህርይ አላቸው ወይ? የሚል ጥያቄ አንስተዋል፡፡

9. **የይገባኛል ጥያቄዎች** (claims):- አንድ በዘርፉ የተሰማሩ የኮንስትራክሽን ሕግ ምሁር ያስቀመጡትን ‹‹claims in a construction industry is an industry within industry›› በሚል የቀጠሉት አቶ ፋሲል የኮንስትራክሽን ውል ልዩ የሚያደርገው ሌላኛው ጉዳይ ውሉ እራሱ ያለመግባባት ወይም የይገባኛል ጥያቄዎች (grounds and causes of claim)የሚመነጩት ከምን እንደሆነ እና መፍትሔዎቻቸውን (remedies thereto) ማስቀመጡ ልዩ ያደርገዋልብለዋል፡፡ የመንግሥት ግዥና አስተዳደር ኤጀንሲ ባወጣው ስታንዳደርድ ላይ claims arising under contractን ካስቀመጠ በኋላ መፍትሔውንም ቀጥሎ ያስቀምጣል፡፡ በግንባታ ውሎች ውስጥ አለማግባባት የማይቀርና የሚጠበቅ መሆኑንየጠቀሱት አቶ ፋሲል ዋናው ቁምነገር ግን የdispute settlement procedure በአግባቡ መቀመጡ ነው ብለዋል፡፡

10. **አለመግባባት ስለሚፈታበት መንገድ** (claim settlement mechanism):- በኮንስትራክሽን ሥራዎች እና ውሎች ላይ ግጭቶች መኖራቸው ችግር የሌለው ሲሆን ቁም ነገሩ እነዚህን አለመግባባቶችየሚፈቱበት አግባብ ወይም መንገድ መኖሩ እንደሆነ አቶ ፋሲል አስምረውበታል፡፡ አማካሪ መሃንዲስ መንታ ባህርይ (twin character) እንዳለው ያብራሩት አቶ ፋሲል አማካሪ መሃንዲስ (Consultant Engineer) አንድም የአሰሪው ወኪል (client agent) ሲሆን አንድም በአሰሪውና በተቋራጩ መካከል ግጭትና አለመግባባት ሲኖር እንደ ግጭት ፈች ገላጋይ ዳኛም የሚሰራ መሆኑን፤ እንዲህ ዓይነቱ አሠራር ለኮመን ሎው ሀገራት የሚገርም ባይሆንም በኮንቲኔንታል ሎው ሀገራት ግን የተለየ መሆኑን፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ በኮንቲኔንታል ሎው ሀገራት የdispute adjudication board እና የdispute review board መኖራቸውንም ጠቁመዋል፡፡

### <u>አቶ ዜና ደባሱ - አወያይ /የሕግ አማካሪና ጠበቃ እንዲሁም በመስኩ የረዥም ጊዜ ልምድ ያላቸው ባለሙያ/</u>

አወያዩ አቶ ዜና ደባሱ ፅሁፍ አቅራቢውን አመስግነው በገለጻው በተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች ላይ በሰጡት በፅሁፉ መግቢያ ላይ የተጠቀሰው የዓፄ ቴዎድሮስን ቀልብ የሳበው የሠሪ፣ የደንጓሪ እና

የአነዋሪ ሥራ ሥርዓት አሁን ድረስ የምንጠቀምበት የአሠሪ፣ የተቋራጭ እና የአማካሪ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ መሆኑን ጠቁመው የአስተዳደር ውልን በሚመለከት ተፈፃሚ የሚሆነው ሕግ የፍ/ብሔር ሕጉ አንቀፅ 3131 እና ቀጣዮቹ ላይ ተደንግጎ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

የኮንስትራክሽን ውሎች የተለያዩ አካላት የሚሳተፉበት መሆኑን እነዚህም የarchitecture design, የsanitary, የኤሌክትሪካል፣ የመካኒካል ስራዎች፣ የጨረታ ማስያዣ፣ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና፣ ቢል ኦፍ ኳንቲቲ፣ የኳንቲቲ ሰርቬይ፣ የመድህን ድርጅቶች ተሳትፎ፣ የንዑስ ተቋራጭ ድርጅቶች ሥራዎችን ለማቀላጠፍ የሚገቡበትን ሁኔታን አስታውሰዋል፡፡ የግንባታ ውል ሌላው የሚለየው ነጥብ ከመለዋወጥ (variations) ጋር የተያያዘው መሆኑንም አንስተውላለፉት ዓመታት የግንባታ ወይም የሲቪል ሥራዎችን የሚያሰራው አሰሪው መንግሥት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አብዛኛውን ጊዜ በነዚህ መ/ቤት ውስጥ በቅጥር የሚሰሩ መሃንዲሶች በአቅም ደረጃ ብቁ ባለመሆናቸው የዲዛይን እና ሌሎች የሥራ ለውጦች በተከታታይና በየጊዜው የሚታዩ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

የግንባታ ውል እና ሥራ በባሕርይው አደጋዎች ወይም ሪስክ የበዛበት መሆኑንያወሱት አወያዩ ጉዳዩን ለማበራራት ጊዮን ሆቴል አካባቢ ያለው ባለ16 ፎቅ ሕንፃ በምሳሌነት በመጥቀስ አንድ ባለሙያ የሕንፃው ስትራክቸርን አስመልክቶ ስፍራው የዕሳተ ጎመራ (volcanic) ባሕርይ ያለው መሆኑን፣ በአካባቢው ወንዝ መኖሩን፣ ብዛት ያላቸው ተሽከርካሪዎች ከስር በፍጥነት የሚበሩበት መሆኑን ፣ አሁን ደግሞ የባቡር መስመሩም ባጠገቡ የሚያልፍ መሆኑ በአካባቢው ያለው ንዝረት (vibration) ችግር ሊፈጥር እንደሚችል በመዘርዘር በሕንፃው ዲዘይንና መዋቅር ላይ ጥያቄ ያነሳ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የኮንስትራክሽን ውል ሰፊና ብዙ ሰነዶችን የሚይዝ መሆኑ ሌላኛው ልዩ መገለጫው መሆኑን አቶ ዜናአስቀምጠዋል፡፡ እ.አ.አ. ከ1987 ወዲህ ነው ***Fédération Internationale Des Ingénieurs-Conseils***(FIDIC) ላይ ያለው standard conditions of contract for Civil project በሚል ያለን ያሉት አወያዩ አቶ ዜና ተቋራጩና አሠሪው ውል ሲገቡ ይሄ ስታንዳርድ የውሉ አካል እንደሆነ አድርገው ይዋዋላሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ስታንዳርድ ኮንዲሽን ደንብ ነው? መመሪያ ነው? በሕግ ፍረጃ (Classification) የትኛው ደረጃ ላይ ነው የሚቀመጠው? የሚሉ ጥያቄዎችን አንስተዋል፡፡ ሌላው በኮንስትራክሽን ውሎች ውስጥ claim ሁሌም የሚኖር መሆኑን አስታውሰው ሲኤምሲ በመባል የሚታወቀው ቦታ ከጣሊያን የግንባታ ሥራ ተቋራጭ ስም ጋር ተያይዞ የመጣ ስያሜ መሆኑን ገልፀው ተቋራጩ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ የclaim manager ይዞ መጥቷል በማለት claim ምን ያህል ድርሻ እንዳለው አወያዩ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ በሱማሌ ጦርነት ጊዜ የድሬደዋ ኤርፖርትን

በጊዜያዊነት እንደ ሚሊታሪ ኤርፖርትነት ስንጠቀም የነበረ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ዜና አንድ ተዋጊ ጄት ከኤርፖርቱ ተነስታ ወደ 2 ኪሎ ሜትር ግድም እንደተጓዛች የማይገባ ቦታ የተቀመጠ ቦምብ ተንሸራቶ ወድቆ የፈጠረው ንዝረት የአየር ማረፊያውን አንድ የግንባታ ክፍል ጣሪያ ሙሉ ለሙሉ እንዲወድቅ ምክንያት የነበረ ሲሆን ዲዛይነሩ ሕንፃውን የሰራው (workman) መበየድ የሚገባውን ቦታ ባለመበየዱ ጉዳቱ እንደደረሰ ሲከራከር፤ ሰሪው መሃንዲስ ደግሞ ቦታው መበየድ እንዳለበት የሚያስቀምጥ ነገር በዲዛይኑ ላይ ባለመኖሩ ምክንያት እንዳልበየደና ይህ ሥራ እንዲሰራ ዲዛይነሩ በዲዛይኑ ላይ ያላስቀመጠ በመሆኑ ለጉዳቱ ምክንያት ዲዛይነሩ ነው በሚል የተከራከረ መሆኑን፤ ዲዛይነሩ በበኩሉ ሁሉም ዓይነት ሥራ በዲዛይን ላይ የማይቀመጥ መሆኑን ጠቅሶ ቦታውን መበየድ የሠሪው መሃንዲስ የሙያው ግዴታ እንደሆነ ጠቅሶ የተከራከሩበት ሁኔታንበማንሳት  ቀደም ብሎ የነበረው traditional contract ቀርቶ በdesign and buildየተተካ መሆኑን፤ አሁን ይህ ዓይነት መወነጃጀል እንደሌለ አወያዩ አስቀምጠዋል፡፡ በኮንስትራክሽን ውሎች ላይ በአሰሪውና በተቋራጩ መካከል ለሚፈጠር አለመግባባት አማካሪ መሃንዲሱ እንደ ገላጋይ ዳኛ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ እንደሆነ አደርገው ስምምነት ይፈፅማሉ ያሉት አቶ ዜና በቀረበው ጽሑፍ ላይ ጥያቄና አስተያየት እንዲሰነዘርበት መድረኩን ለቤቱና ለታዳሚው ክፍት አድርገዋል፡፡

<u>**አቶ -----------   ------------- (ስማቸው ያልተጠቀሰ )**</u>

በሀገራችን ብዛት ያለው የኮንስትራክሽን ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን በዚሁ መጠን ደግሞ በየቦታው የተሰሩ ሥራዎች የሚፈርሱበት፣ የሚቆፈሩበት ወይም ተደጋጋሚ ጥገና የሚሹበት፣ ሕንፃዎች የሚዘሙበት ሁኔታ ያለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሀገራችን ሕግ የጥራት ቁጥጥርን (quality control) የሚመለከት ምን ነገር አለው?

<u>**አቶ --------------- - ከደረጃ 1 የሥራ ተቋራጭ ማሕበር**</u>

የቀረበው ገለጻ እጅግ በጣም ጥሩ እንደሆነ ገልፀው ጽሑፍ አቅራቢውን፣ አወያዩን እና አዘጋጆችን ካመሰገኑ በኋላ ወደ ጥያቄ ያመሩ ሲሆን ጥያቄዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ያወጣቸው መመሪያዎች አሉ የራሳቸው ጋይድላይን አላቸው፡፡ ሁሉም ጠቅላላ የውል ሁኔታዎች (General Conditions of Contract) ወደ ልዩ ሁኔታዎች (special conditions of contract) እየተቀየሩ ነው፡፡ ይሄ አግባብ ነው?
- የሕግ አተረጓጎም ጋይድላይን በእኛ ሀገር ለምን አይዘጋጅም? በትርጉም ምክንያት 3ቱም አካላት ማለትም አሠሪው፣ ተቋራጩና አማካሪው በተለያየ መንገድ ይተረጉማሉ፡፡ ይህ ደግሞ ለግጭት ምክንያት ይሆናል የአተረጓጎም ማንዋል ለምን አይወጣም?

## አቶ ፋሲል ታደሠ - ጽሑፍ አቅራቢ

በተነሱት ጥያቄዎች ላይ ምላሽ ለመስጠት መድረኩን መልሰው የተረከቡ ሲሆን የኮንስትራክሽን ውል ወይም ሕግ እጅግ ሰፊና ውስብስብ መመሆኑን፤ የዕለቱ ውይይት ደግሞ የBuilding and Design Construction Contract ላይ መሆኑን አስታውሰዋል። በNational Urban Planning Institute የአካባቢ ደህንነት (environmental safety) መጠበቅ እንዳለበት ይቀመጣል። Quality maintain የሚደረግበት የራሱ መስፈርቶች ያሉ ሲሆን በሚባለው መስፈርት ይሰራሉ ማለት ግን ከሁኔታ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል ብለዋል። በአዋጁ ላይ የquality testing እንዳለም ጠቁመዋል።

የመንግሥት ግዥና አስተዳደር (PPA)ያወጣው ስታንዳርድ አለ ይህ ሕግ አይደለም:: General condition ለspecial ሥራ customize ሊደረግ የሚችል መሆኑን ገልፀው ይህ ጠቅላላ ሁኔታ የሁለቱንም ወገን ጥቅምና መብት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ risk allocate የሚያደርግ ነው። ይሄ General codition ወደ አንድ ፕሮጀክት ሲሄድ እንደ ሥራው ባህርይ እንዲስማማ /best fit/ ተደርጎ ይዘጋጃል። FIDIC standard ይሁን እንጂ የሀገር ውስጥ ሕግ ነው የሚዳኘው። እነዚህ ሁኔታዎች ወደ specific project ሲቀየር የሚመከረው ሙሉ ለሙሉ መቀየር ሳይሆን change whenever change is necessary የሚለውን መርህ መሰረት አድርጎ መሆን እንዳለበት አስቀምጠዋል።አማካሪ መሃንዲስ (consultant engineer) እንደ ዳኛ ሲሆን በራሱ ጉዳይ ወይም የራሱ ጥቅም ያለበትን ጉዳይ ሊያይ የሚችልበት አጋጣሚ መኖሩን ይሄ ደግሞ ‹‹one cannot be a judge in his own case›› የሚለውን መርህ የሚጣረስ ነው ብለዋል አቶ ፋሲል።

## አቶ ዜና ደባሱ - አወያይ

General standard ወደ 72 ድንጋጌዎች የያዘ ሲሆን ይህ ሰነድ ግጭቶችን ለመፍታት የምንገለገልበት መሳሪያ መሆኑን፤ ወደ ፕሮጀክት ሲገባ ወደ ልዩ ሁኔታ እንደሚቀየር አቶ ፋሲል ተናግረዋል።አያይዘውም በሆነ ወቅት ላይ advance paymentን የሚከለክል በአንፃሩ የperformance bond percentageን የሚጨምር ወይን ከፍ የሚያደርግ ሁኔታ ተፈጥሮ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ፋሲል ቅድመ ክፍያ በመከልከል የሥራ አፈጻጸም ዋስትናን ከፍ ማድረግ የተቋራጮችን አንድ እጅ ማሰር እንደሆነ፤በዚህ ምክንያት particular condition እንዲወጣ መደረጉን ጠቁመዋል። የጥራት ቁጥጥርን በተመለከተ ግንባታ ፈቃድ የሰጠው አካልና consultant engineer ኃላፊነት አለባቸው ተቋራጩም እንዲሁ ብለዋል።

**ወ/ሮ ሐመረ ተሾመ - ከኢትዮ ቴሌኮም**

ከኮንስትራክሽን ስራ ጋር በተያያዘ በመ/ቤታችን በሕግ በማማከር የተሳፍኩ ሲሆን የቀረበው ፅሁፍ ጥሩ እንደሆነ በመግለፅ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቅርበዋል፡፡

- Variationን በተመለከተ ሕግም ውልም ላይ ይቀመጣል፡፡ በውል ላይ completion date ቢኖር ምን ይሆናል? Completion date vary ቢያደርግ በገንዘብ ብቻ ነው የሚገለጸው ወይስ ተጨማሪ ቀን (extension) መጠየቅስ?
- Force majeure ጋር በተገናኘ completion date በFIDIC ላይ አሠሪው ወጪውን ይችላል ወይ?
- ንዑስ ተቋራጭ በአሰሪው ወይም በተቋራጩ ተመርጦ ውል ሊይዝ ይችላል፡፡ የንዑስ ተቋራጭ ተጠያቂነት ለማን ነው?
- Admeasurement and lumpsum contract ላይ essential parties እነማን ናቸው? በምንስ ይለያያሉ?
- የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር እና በሥራና ከተማ ልማት የወጡ ስታንዳርዶች ያሉ ሲሆን መ/ቤቶች የየራሳቸውን ስታንዳርድ ማውጣት ቢፈልጉ የትኛው ይመከራል?
- General Condition of Contract የውል አካል ሆኖ ሲጠቀስ በተዋዋይ ወገኖች መፈረም አለበት?

**አቶ ፋሲል ታደሠ - ጽሑፍ አቅራቢ**

በተነሱት ጥያቄዎች ላይ ምላሽ ለመስጠት መድረኩን መልሰው የተረከቡ ሲሆን GCCን የውሉ አካል ለማድረግ በግልፅ ከተጠቀሰ በቂ እንደሆነ አስረድተው በሀገራችን ካሉ GCCዎች የትኛው ይመከራል ለሚለው ምላሽ ሲሰጡ አንደኛው ከሌላኛው የተሻለ ነው የሚባል ነገር ባይኖርም ዋናው ቁምነገር ውሎቹን በአግባቡ ማስተዳደር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ የcompletion date ጋር የተያያዘው ጥያቄን በሚመለከት ውል በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚገኝ እንደ ሕግ ሆኖ የሚያገለግል በተዋዋይ ወገኖች ላይ መብትና ግዴታን የሚያስቀምጥ የprivity of contract መርህ ስላለ ይህንኑ በመጠቀም በውል መወሰን የሚቻል መሆኑን አብራርተዋል፡፡ በadmeasurement እና lumpsum contract ን በተመለከተ ሁለቱም በፍትሃብሔር ሕጉ ላይ የተቀመጡ ክፍያ የሚፈፀምባቸው መንገዶች ሲሆኑ የመጀመሪያው በየጊዜው የሥራው ባሕርይ እየተለካ በዚሁ ልክ ክፍያ የሚፈፀምበት አግባብ ሲሆን ሁለተኛው ግን ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው የቁርጥ ክፍያ ቀደሞውኑ በውል ተወስኖ የሚቀመጥበት ሁኔታን ለመግለፅ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ completion date vary ቢያደርግ በገንዘብ ብቻ ሳይሆን የሚገጸው ተጨማሪ ቀን (time extension) መጠየቅንም ይጨምራል፡፡

በtraditional contract ላይ defect የተፈጠረው በdesign ነው ወይስ በworkmanship ነው የሚለው ብዙ ጊዜ አንዱ ሌላኛውን አጥፊ ነው ይላል አሁን ግን design and build arrangement በመምጣቱ ቀደም ብሎ የነበረውን interplay(ምልልስ) ያስወግዳል ብለዋል፡፡

<u>**አቶ ዜና ደባሱ - አወያይ**</u>

የተነሳው ጉዳይ ለሥራ መለዋወጥ (variation) ኃላፊው ማን ይሆናል ለሚለው ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ከሌለ በቀር ለሥራው መለወጥ ምክንያት የሆነው ሰው እራሱ በለውጡ ምክንያት ለሚመጣው ወጪ ኃላፊነት ይወስዳል ካሉ በኋላ በምሳሌነት ሰኔ ላይ ዝናብ አስቸገረኝ የሚለው foreseeable ስለሆነ ተቀባይነት እንደሌለው፤ ነገርግን ታህሳስ ላይ ዶፍ አስቸገረኝ የሚለው የተለመደ ባለመሆኑ ሊያስኬድ እንደሚችል ግልጽ አድርገዋል፡፡ ሌላኛው መ/ቤቶች የራሳቸውን ስታንዳርድ ቢያወጡስ ለሚለው የማይስማሙ መሆኑን ገልፀው ይህን ስራ እንዲሰራ ኃላፊነት ተሰጥቶት የተቋቋመ አካል አለ ብለዋል፡፡

በadmeasurement ውል ጋር በተያያዘ ሁለት ተጨባጭ ምሳሌዎችን በማንሳት ገለፃ ያደረጉት አቶ ዜና የመጀመሪያው ከመራቤቴ ሰቆጣ የተሰራውን የመንገድ ዝርጋታ ፕሮጀክት እነደነበር የቦታው ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ለመንገድ ግንባታ የማይመጭ ጠቅላላ በጀቱን እንኳ ለማስላት አስቸጋሪ በነበረበት ወቅት በወቅቱ ከሀገራችን የመንገድ ግንባታ ሥራ ጋር በተያያዘ ብዙ አስተዋጽዖ ያበረከቱ አቶ ካሡ የሚባሉ ሰው መንገዱ መሠራት እንዳለበትና የሚሰራውም እንደሥራው ወጪ መጠን እየታየ እንጂ በቁርጥ ክፍያ የማይቻል መሆኑን በመገንዘብ የሥራ ክፍያውን ወጪ ሲደመር የትርፍ ማርጅን በማስላት ግንባተው እንዲከናወን የተደረገበት አግባብ እንደነበር አስታውሰዋል፡፡ ሌላው የጠቀሱት ምሳሌ በደቡብ ክልል ውስጥ የተሰራ የመንገድ ግንባታን ሲሆን የመንገዱን መሠረት ለመስራት በሚደረገው ቁፋሮ በአንድ አንድ ቦታዎች ላይ ሰፊ ጉልበት እና ገንዘብ የሚጨረስ፤ በሌሎች ቦታዎች ላይ ደግሞ አንፃራዊ የሥራ ቅለት በመኖሩ ምክንያት በቁርጥ የሚደረግ ክፍያ አግባብ አለመሆኑ የተቀመጠበት ሁኔታ እንደነበረ አብራርተዋል፡፡

ከግልግል ዳኝነት ጋር በተያያዘ በአንድ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ከኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ጋር አለማግባባት በመፍጠር ክርክር የገቡበት አጋጣሚንም በምሳሌነት ያነሱት አቶ ዜና ሁኔታውን ሲያብራሩ ለገሃር ተነስቶ በቸርችል አድርጎ የሚመጣው መንገድ በቀጥታ ከከተማ መስተዳደሩ መቀመጫ በተለምዶ ማዘጋጃ ቤት ከሚባለው ህንጻ ጋር እንዱገናኝ ተፈልጎ ዲዛይን ከተሰራ በኋላ ሥራው ሲጀመር በቁፋሮ ምክንያት ንብረትነቱ የቴሌ የሆነ ኬብል በመቆረጡ ምክንያት

አለመግባባት ተፈጥሮ በመሃል አስታራቂ ገብቶ ጉዳዩ በእርቅ ያለቀ ቢሆንም መንገዱ ግን ሳይሰራ ቀርቷል ብለዋል፡፡

<u>አቶ ፋሲል ስለሺ - ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኀበር</u>

አማካሪ መሃንዲስ የሚሰጠው የግልግል ዳኝነት ውሳኔ (arbitral award) ገዥና የመጨረሻ መሆኑን በስምምነቱ ላይ designate አድርገዋል፡፡ ይሄ አካል የሚሰጠው ውሳኔ በራሱ ጉዳይ ላይ ጭምር ሊሆን እንደሚችል በመጥቀስ ‹‹አንድ ሰው የራሱ ጉዳይ ላይ ዳኛ መሆን አይችልም›› ከሚለው መርህ ጋር የሚጣረስ እንደሆነ የተገለፀ ይሁን እንጂ ‹‹a contract is a law among the contractants›› በሚለው ተስማምተው የራሱም ጥቅምም ቢኖርበት እንዲያይ በውል አሳልፈው ከሠጡት ምኑ ነው ችግሩ? ሌላው የሠራተኞች ኃላፊነት አልተሸፈነም ወይ?

<u>አቶ ፋንታሁን መንግስቴ - የሕግ አማካሪና ጠበቃ</u>

Designand build arrangement ዘመናዊ የውል ዓይነት መሆኑ ይታወቃል፡፡ የመንግሥት ሥራዎች ሲሆን መንግሥት የራሱ አማካሪ መሃንዲስ ስላለው ችግር የለም ነገር ግን የግል ሥራዎች ሲሆኑስ ምን ይደረጋል?

<u>አቶ ታከለ ጎንፍ - የሕግ አማካሪና ጠበቃ</u>

በአሠሪው እና በተቋራጩ መካከል ውል እንዳለ ይታወቃል፡፡ አማካሪው ከማን ጋር ነው ውል የሚገባው? ኃላፊነቱስ?

<u>አቶ አያሌው ቢታኔ - የሕግ አማካሪና ጠበቃ</u>

ውይይቱ የወፍ በረር እንደነበረ ገልጸው ፕሮግራሙ የኮንስትራክሽን ውል በዝርዝር ቢሆን በማለት ለውይይት ሊሆኑ የሚችሉ ነጥቦችን ለመዘርዘር የሞከሩ ሲሆን እነዚህም የግንበታ ውል፣ የግንባታ ሕጎችና ውሎች አተረጓጎም፣ የኮንስትራክሽን ፖሊሲው፣ የግንባታ ውል ግንኙነት ላይ ያለው የይገባኛል ጥያቄዎች እነ እነዚህ አለመግባባቶች የሚስተናገዱበት አግባብ ወዘተ ሆነው በስፋት ብነወያይበት መልካም ነው ካሉ በኋላ ወደ ጥያቄያቸው ያለፉ ሲሆን ያነሱት ነጥብም የአስተዳደር ውሎች በግልግል ዳኝነት መታየት የማይችሉ ስለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ ያስቀምጣል አሁን ደግሞ መንግሥት በሚያሰራቸው ሥራዎች ላይ ስለግልግል ዳኝነት እየተነገረ ነውና procedural law ከsubstantive ሕጉ ጋር ሲጣረስ ምን ይሆናል?

## አቶ ፋሲል ታደሠ - ጽሑፍ አቅራቢ

በመርህ ደረጃ ተዋዋይ ወገኖች የውል ነፃነት (freedom of contract) አላቸው፡፡ standard condition of contract ላይ አማካሪ መሃንዲስ አሰሪውን ይወክላል፡፡ ይህ አማካሪ ማሃንዲስ የሚሰጠው ውሳኔ ወደ adjudicator ከዚያም ወደ arbitration ይመጣል፡፡ እነ ዓለም ባንክ Dispute Board እንዲቋቋም ያደርጋሉ፡፡ አንድ ሰው ፍትህ የማግኘት መብት ያለው ሲሆን ፍርድ ቤቶችም የዳኝነት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ አማካሪ መሃንዲስ የአሠሪው ወኪል ሆኖ ቢቀርብም ብዙ ጊዜ ውሉ ላይ እንደ ተዋዋይ ወገን ሳይሆን እንደ ምስክር ሆኖ በውሉ ላይ ፈርማል ብለዋል፡፡ በአሰሪው ክሊያንት እና በተቋራጩ መካከል የሥራ ውል አለ፡፡ በሌላ በኩል በአሠሪው እና በአማካሪ መሃንዲሱ መካከል ውል አለ፡፡ ነገር ግን በአማካሪውና በተቋራጩ መካከል ግን ውል የሌለ በመሆኑ በመካከላቸው ግጭት ወይም አለመግባባት ቢፈጠር ከውል ውጭ ኃላፊነት መሠረት ይጠያየቃሉ በማለት አብራርተዋል፡፡

## አቶ ዜና ደባሱ - አወያይ

የፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀፅ 1731 ውል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሕግ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑን ይጠቅሳል በአንፃሩ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 315 ደግሞ በአስተዳደር ውሎች ላይ አለመግባባቶች በግልግል የዳኝነት ሥርዓት እልባት መስጠት የማይቻልና ሕጋዊ ውጤት እንደሌለው ያስቀምጣል፡፡ ተዋዋይ ወገኖች በአስተዳደር ውላቸው ላይ ግጭቶችን በግልግል የዳኝነት ሥርዓት ለመፍታት ይስማማሉ በዚህን ጊዜ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ጋር ይጋጫል፡፡ ብዙ የመንግሥት ፕሮጀክቶች የሚከናወኑት ከውጭ ሀገር በተለይም ከዓለም ባንክ በሚገኝ እርዳታ ሲሆን እነዚህ የውጭ ተቋማት ደግሞ arbitration clause እንዲኖር ይፈልጋሉ፡፡ የarbitration clause ከውል እንዲወጣ ብናደርግ እርዳታውን ለመከልከል ምክንያት እንደይሆን በሚል arbitration clause እንዲገባ ይደረጋል፡፡ በፍርድ ቤቶች በኩል ደግሞ በarbitration የተገኘ arbitral awardን የማይቀበሉመሆኑን አወያዩ አቶ ዜና አብራርተዋል፡፡

## አቶ ወንድሙ ኢብሳ - የሕግ አማካሪና ጠበቃ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ብዙም አይሰማም ብዙ መስራት አለበት ካሉ በኋላ የተዘጋጀው መድረክ እጅግ በጣም ጥሩ ነው የሚል አስተያየት ከሰጡ በኋላ ወደ ጥያቄያቸው ያለፉ ሲሆን በጅምር ላይ ያሉ ሰዎች በአግባቡ ሳይጠናቀቁ ሥራ የሚጀምሩበት አግባብ በተግባር እንዳለ ይታወቃል፡፡ አዋጁ ደግሞ ሕንፃ ሳይጠናቀቅ ሥራ መጀመር እንደሌለበት ይደነግጋል፡፡ ይሄ ጉዳይ እንዴት ነው የሚታየው?

## አቶ ፋሲል ታደሠ - ጽሑፍ አቅራቢ

የሕንፃ ሕጉ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ሕንፃዎች ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት ተጠናቀው ማለቅ እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ የሚያስቀምጥ መሆኑና ሳይጠናቀቁ ሥራ እንዲጀምሩ የሚፈቀዱት በልዩ ውስን ሁኔታዎች እንደሆነ አስቀምጠው በተግባር ግን ይሄ ችግር እንዳለ በሶስተኛ ወገን ላይ ጉዳጥ የሚደርስበት ሁኔታ የሚስተዋል መሆኑን ገልፀው ያጠቃለሉ ሲሆን መድረኩን ለአዘጋጁ የማኅበሩ አመራሮች ሰጥተዋል፡፡

## አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዝዳንት

የማህበራችን እድሜ ሁላችንም እንደምናውቀው ትልቅ ይሁን እንጂ እንደ እድሜው መስራት የሚገባንን ያህል ሰርተናል ማለት አይቻልም፡፡ የማኅበሩ ጥንካሬ የአባላቶቹ እንዲሁም በሙያው የሚሰሩ ሰዎች ጥንካሬ ላይ የሚመሰረት በመሆኑ አባላቱ የሚገባንን ሚና በአግባቡና በላቀ ሁኔታ መወጣት እንዳለብን ብለዋል፡፡ ወርሃዊ መዋጮ በመክፈል፣ የበጎ ፈቃድ ስራዎችን በመስራት እና ወደ ማህበሩ ቀርቦ መስራት የማኅበሩ እድገት ላይ በጎ ተፅዕኖ ማሳደር ይቻላል ያሉት የማኅበሩ ፕሬዝዳንት ምንም እንኳን በአመራርነት የማገልገል ጊዜያቸው እያለቀ ቢሆንም በሁሉም የሕግ ዘርፎች ቋሚ ኮሚቴዎችን በማዋቀር ላይ የምነገኝ ሲሆን አባላቱም በምርጫቸው በንዑስ ኮሚቴዎቹ ተሳታፊ በመሆን የበኩላችሁን አስተዋፅዖ ማበርከት መቻል አለባችሁ አለብን ብለዋል፡፡ ይሄ የሁልጊዜ የቤትሥራችን ነው፡፡ የclaim writing ላይ workshop ይኖረናል የሁላችሁም ተሳትፎ ያስፈልጋል በማለት የማህበሩን ዳይሬክተር እና ቃለጉባዔ ፀኃፊ አመስግነው መድረኩን ለቀጣይ የማኅበሩ ፕሬዝዳንት ለሚሆኑት ለአቶ ቴዎድሮስ ምህረት መድረኩን ሰጥተዋል፡፡

## አቶ ቴዎድሮስ ምህረት - የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር
## የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል እና የማኅበሩ እጩ ፕሬዝዳንት

በዕለቱ የተደረገው ውይይት ስለ ኮንስትራክሽን ነው ግንባታ ያለbuilding blocks እና bricks ዋጋ እንደሌለው ሁሉ የማኅበሩም ሁለንተናዊ ጥንካሬና ተፅዕኖ ፈጣሪነት በአባላቱ ላይ የተመሠረተ መሆኑን አባላቱ በአባልነት ኃላፊነት መወጣት፣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ በመሳተፍ እና ጆርናል ላይ ፅሁፍ በማውጣት መሳተፍ የሚቻል መሆኑን ለታዳሚው ያሳወቁት አቶ ቴዎድሮስ ቀጥለውም በውጭ ሀገራት ጠበቆች በፍርድ ቤቶች ውስጥ የራሳቸው ማረፊያ ቢሮ እንዳላቸው፣ የፍ/ቤት ሕንፃዎች ሲሰሩ ይህን ታሳቢ ያደረጉ ሲሆኑ በእና ሀገር ግን አሁን የሚሰሩ ሕንፃዎች እንኳ ይህ ዓይነት ነገር የሌላቸው መሆኑ ለእኛ ሊሰጠን የሚገባው ክብርን እንኳ ለማስጠበቅ ያለመቻላችን

ማሳያ መሆኑን ጠቁመው ማኅበሩ በሙሉ አቅሙ የሚነቀሳቀሰው በአባላቱ የነቃ ተሳትፎ እንደሆነ አሳስበው አጠናቀዋል፡፡

## <u>አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙዎች ማኅበር ፕሬዝዳንት</u>

በመጨረሻም አቶ ታምራት መድረኩን ተረክበው በዕለቱ በነበረው ውይይት ለብዙ አካላት ጥሪ ተደርጎ የነበረ መሆኑን ጠቅሰው ከነዚህ መካከልም የሕ/ተወካዮች ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፣ የአዲስ አበባ መንገዶች ቢሮ፣ የሥራና ከተማ ልማት፣ የአርኪቴክቸር ማኅበር፣ የደረጃ 1 የሥራ ተቋራጭ ማህበር ወዘተ ተጠቃሽ እንደሆኑ ገልፀው ለተሳታፊዎች በሙሉ ጥሪውን አክብረው በመምጣታቸው አመስግነው፣ ጽሁፍ አቅራቢውንና አወያዩንም በድጋሚ ካመሰገኑ በኋላ ምንጊዜም የቤቱ ተሳትፎ እንዳይለያቸው ጠይቀዋል፡፡ ውይይቱ ከቀኑ 7፡00 ሠዓት ተጠናቋል፡፡

////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////